# ጃዋር መሐመድ የወያኔ ሰላይ መሆኑን ያውቃሉ???

**10/08/2016**

የማኅበራዊ የብዙኃን መገናኛውን ሀገራዊ ጉዳይን ለመከታተያነት ከሚጠቀሙ ዜጎች ጃዋር መሐመድን የማያውቅ ብዙ ያለ አይመስለኝም፡፡

ጃዋር መሐመድ "የወያኔ ሰላይ ነው!" ስል ከጥቂቶች የሰውየውን ማንነት ከሚያውቁ ወገኖች በስተቀር የተቀረው ክፍል በእርግጠኝነት ከጥላቻ ተነሥቸ ስም ለማጥፋት የማወራው ወሬ እንጅ እውነት አይመስላቸውም፡፡

እነኛ ጥቂት ያልኳቸው ወገኖች ግን ከሰውየው የጀርባ ታሪክ ተነሥተው፣ ማንን እንዲሰልልና ወደ ኦነግ ሰርጎ ገብቶ ምን ግብ እንዲመታ እንደታሰበ፣ ጃዋር ለማስመሰልና በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ተአማኒነት ለማግኘት የሚሠራውን ወያኔን ተጠቃሚ ለማድረግ ከሚሠራው በመለየት እያንዳንዷን የሚፈጽማትን ተግባሩን በሚገባ በመመርመር ከወያኔ የተሰጠውን ተልዕኮ ተረድተው የሰውየውን ማንነት በሚገባ ያውቃሉ፡፡ ወደፊት በዚህ ጉዳይ ላይ በመረጃ ከተደገፈ ሰፊ ማብራሪያ ጋር እንመለስበታለን፡፡

ለዛሬ ግን ለጥቆማ ያህል አንድ ልጥቀስላቹህ፡፡ ሰሞኑን ጃዋር "የኦሮሚያ ነጻ መንግሥት የመመሥረቻ ቻርተር" ሲል ስለተናገረው ጉዳይ ገዘፍ ያለ ወሬ ማውራቱ ይታወሳል፡፡ ወያኔ ይሄንን ጃዋር ያወራውን ከኦነግ አመራሮች ጆሮ እንኳን በቅጡ ያልተሰማንና በዚህ ደረጃ ያልተወያዩበትን ጉዳይ በዚህ ሰዓት በድንገት ጃዋርን እንዲያወራ ያደረገበት ምክንያት፡- እንደምታዩት በሀገሪቱ እየተደረጉ ባሉ ሕዝባዊ ዐመፆች ወያኔ ጽኑ በሆነ የነፍስ ውጪ የነፍስ ግቢ ጭንቅ ጥብ ላይ ወድቆ ይገኛል፡፡ በዚህም ምክንያት በተለይ የአማራና የኦሮሞ ሕዝብ በዚህ ደረጃ በአንድነት እያደረግን ያለነውን የተባበረ የአንድነት ፀረ ወያኔ ግዙፍ ሕዝባዊ ዐመፅ መነጠል መለየት መስበርና ማዳከም በእጅጉ ይፈልጋል፡፡ ይሄንንም ለማድረግ የአማራና የኦሮሞ የእርስ በእርስ የዘር ግጭት ለመፍጠር ከማሴር ጀምሮ በርካታ የተለያዩ ሙከራዎችን ሲያደርግ ቢቆይም ሕዝቡ በመንቃቱና ሴራውን በመከላከሉ መሰንበቻውን የደከመበት ሴራ ሊሠምርለት ሳይችል ቀርቷል፡፡

ይህ ወያኔ በጃዋር በኩል ያፈነዳውና በዚህ ወቅት ላይ የነፍስ ውጪ የነፍስ ግቢ ጭንቅ ጥብ ላይ የጣለውን "የአማራና የኦሮሞ የአንድነት ሕዝባዊ ዐመፅ ጥምረትን ይለያይልኛል፣ ያፈርስልኛል፣ የኦሮሞን ሕዝብ ትግል ኢላማ ውስጥ ጥሎ ችግር ላይ ይጥልልኛል እኔም ትንፋሽ ፋታ አገኛለሁ!" ብሎ የተማመነበት ምናልባትም የመጨረሻው ሙከራ ነው፡፡

በእርግጠኝነት መናገር የምችለው ነገር፡- በግልጽ እንደሚታወቀው ምንም እንኳ የኦነግ ዓላማ መገንጠል ቢሆንም አሁን እየተደረገ ያለው የአማራና የኦሮሞ የጥምረት ወይም የአንድነት የተባበረ ፀረ ወያኔ እንቅስቃሴ ግን እንዲፈርስ እንዲከሽፍ እንዲጨናገፍ አይፈለግም፡፡ ጃዋር ለማድረግ የሞከረው ወያኔን ከባድ ጭንቅ ላይ የጣለው የአማራና የኦሮሞ የተባበረ የዐመፅ እንቅስቃሴ እንዲከሽፍ ግቡን እንዳይመታ፣ የኦሮሞ ሕዝብ ትግል በተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ በከፍተኛ በጥርጣሬ እንዲታይና እንዲጠላ እንዲወገዝ ማድረግ ነው፡፡ ማንም ሊገነዘበው እንደሚችለውም ጃዋር በዚህ ተግባሩ ተጠቃሚ ሊያደርገው የፈለገው የቀጠረውን ወያኔን ብቻና ብቻ ነው፡፡

አሁንም እርግጠኛ ሆኘ የምነግራቹህ ነገር፡- ጃዋር እንደሚያወራው ለኦሮሞ ሕዝብ ነፃነት የሚታገል ታማኝ ታጋይ ቢሆን ኖሮ በዚህ ሰዓት እንዲች እንዲች ዓይነቷን ነገር ለጊዜው ዋጥ አድርጎ የአማራውና የኦሮሞው የአንድነት የጥምረት የተባበረ ፀረ ወያኔ ሕዝባዊ ዐመፅ ግቡን እንዲመታ የበኩሉን ጥረትና እገዛ እያደረገ ይቆይ ነበር እንጅ የፈለገውን ያህል ደንቆሮ ቢሆንም እንኳ ይሄንን ወያኔን ጭንቅ ላይ የጣለውን የአማራንና የኦሮሞን ፀረ ወያኔ ጥምረት አንድነት ትብብር ሊያፈርስ ሊለያይ ሊያሻክር ሊያከሽፍ የሚችልን ተግባር በምንም ተአምር በዚህ እጅግ ወሳኝ ሰዓት ሊፈጽም አይችልም ነበር፡፡ ያለው ሀቅ እንዲህ በሆነበት ሁኔታ ጃዋር ይሄንን ያደረገበት ምክንያት ሰውየው ደንቆሮ ቢሆንም ከድንቁርናው አንጻር ሳይሆን ወያኔ የሰጠውን ተልዕኮ ለመፈጸም ብቻና ብቻ ነው፡፡

በዚህ አጋጣሚ ጃዋርን ለማይከተሉት ለነቁበት የኦሮሞ ተወላጆች ሳይሆን ላሳሳታቸው ኦሮሞ ወገኖቻችን ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት ቢኖር ይሄንን ጃዋር መሐመድ የተባለውን የወያኔ ቅጥረኛ ማንነት ለመረዳት ከዚህ በላይ ማሳያ ሊኖር አይችልምና ዐይንና ልባቹህን ከዚህ የወያኔ ቅጥረኛ ላይ አንሥታቹህ እንደ ፕሮፌሰር (ሊቀ ማእምራን) ሕዝቅኤል ጋዲሳ ባሉ ታማኝና እውነተኛ የኦሮሞ ምሁራንና ሌሎች ኃላፊነት የሚሰማቸው ኢትዮጵያውያን ላይ እንድታደርጉ ነው፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com

*http://www.ethiopanorama.com*